# የዶ/ር መረራ ጉዲና ፖሊቲካዊ ፍልስፍና !

October 11, 2017 04:49

ዮሴፍ ሙሉጌታ ባባ, PH.D.*

በኢትዮጵያ ፖሊቲካዊ ፍልስፍና ታሪክ ውስጥ፣ ሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶችን ለ«ማስታረቅ» ከፊተኛ ጥረት ካደረጉ ጥቅት ምሁራን መካከል፣ ዶ/ር መረራ ጉዲናን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ከዝህ በፊት ለንባብ የበቁ የምርምር ሥራዎቹ፣ በአንድነት ኋይሎችና በብሔርተኞች መካከል ያለው እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ ማብቃት እንዳለበት በግልጽ ያሳያሉ— Merera Gudina, Ethiopia: Competing Ethnic Nationalisms and the Quest For Democracy, 1960- 2000, 2002, Passim; Ethiopia: From Autocracy to Revolutionary Democracy, 1960s-2000, 2011, Passim፤ መረራ ጉዲና፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅ ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፣ 2006፣ Passim የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች እና የሚጋጩ ሕልሞች፣ 2008፣ Passim

.

በተለይ፣ የኦሮሞና የአማራ ልሂቃን ፖሊቲካ፣ ብዙም ያለተንቀሳቀሰና «በዋናነት በሁለት ጫፎች ላይ ቆሞ ገመድ ከመጓተት ወደ መሃል መጥቶ የጋራ ዴሞክራትክ አጀንዳ መቅረጽ» እንዳላስቻላቸው ዶ/ር መረራ ያሰምርበታል። (መረራ ጉዲና፣ 2008፣ ገጽ 11) የሁለቱን ልሂቃን ፖለቲካዊ ውይይት አንዱ ሌላውን የማይሰማ «የዶንቆሮዎች ውይይት (dialogue of the deafs)» ሲል አካሄዳቸውን አጣጥሏል። (ገጽ 11፣12) ለወደፊቱ በአፈሪካ ቀንድ ለሚነሳው«ግጭት/ጦርነት» ተጠያቅዎቹ የትግራይ፣ የአማራና የኦሮሞ ልሂቃን መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ የሚከተለውን ሐሳብ በድፍረት ሰንዝሯል፡-

«ለታሪክም፣ ለሕዝብም አስረድቼ ማብቃት የሚፈልገው መሠረታዊ ነጥብ፣ አብዛኛው የትግራይ ልሂቃን ‹ስልጣን ወይም ሞት› ብለው ሥልጣን ላይ የሙጥኝ እስካሉ ድረስ፤ አብዛኛው የአማራ ልሂቃን በአፄዎች ዘመን የነበረውን የበላይነት መልሼ አገኛለሁ ብሎ የሚያስበውን የሕልም ፖሊቲካ እስካልተወ ድረስ፣ ብዙሃኑ የኦሮሞ ልሂቃን ኦሮሚያን ለብቻ የማውጣቱን ሕልም እስካልተወ ድረስ ሀገራችን ከአደጋ ቀጠናና ቀውስ የምትወጣ አይመስለኝም። በሌላ ቋንቋ ለነዝህ መሠረታዊ በሽታዎቻችን መድኃኒት እስካላገኘን ድረስ ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምም ሆነ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ፈጽሞ የምታገኝ አይመስለኝም።» (ገጽ. 12)

ዶ/ መረራ ታሪክና ሕዝብን ለምስክርነት መጥራቱ፣ በኢትዮጵያ ፖሊቲካ ጉዳይ ተስፋ መቁረጡን ያሳያል። «ያ ትውልድ» ካለፈው ጥፋቱ ተምሮ፣ ልዩነቱን አቻችሎና አንድነቱን ጠብቆ ኢትዮጵያን ከመበታተን የሚተዳጋት አይመስለኝም! የዶ/ር መረራ ጉዲናን ምክር መስማት የተሳናቸው መንግስት እና ተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች የጋራ ግንዛቤ እንዳይኖር እንቅፋት እየሆኑ ናቸው። ኢትዮጵያን ከመበታተን ለመታደግ ግን የዶ/ር መረራ ጉዲና መንገድ መከተል አማራጭ የሌለው ነገር ሆኖ እያለ፣ ለፖሊቲካ ፊጀታ ሲባል አሸባሪ በሎ መፈረጅ የበለጠ ያራርቀናል!

ለመሆኑ የዶ/ር መረራ ጉዲና ፖሊቲካዊ ፍልስፍና ምንድን ነው? ከዝ በፊት «ቁም ስቅላችን ያሳየን የኢትዮሮፕያንስ የለየለት ጽንፈኛ አስተሳሰብ» በተሰኘ ርዕስ ሥር ያቀረብኩት ፁሑፍ ጥያቄውን በትክክል ይመልሳል የሚል ጽኑ አቋም አለኝ፡-



ዶ/ር መረራ ጉዲና

የጋራ ግንዛቤ በሌለበት ሀገር/አሀጉር ውስጥ እውነተኛ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ነፃነት መጎናጸፍ ዘበት ነው። ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ የሚቻለው የጋራ ግንዛቤ ሲኖር ብቻ ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ባለመስማማት መስማማት (agreeing to disagree) የሚቻለው አሁንም የጋራ ግንዛቤ ሲኖር ብቻ ነው። በዘመናዊነት ስም የተዘረጋዉ አውሮፓዊነት ግን፣ በአፈሪካዊያን ወይም በኢትዮጵያዊን ማኅበረሰብና ሊሂቃን ዘንድ የጋራ ግንዛቤ እንዳይኖር እንቅፋት ሆኗል። አንድን “ነገር” በመገንዘብ ሂዴት ውስጥ የአተያይ እንቆቅልሽ (puzzles of perception) ወይም የአመለካከት ልዩነት መኖሩ የታወቀ ቢሆንም ቅሉ፣ የአውሮፓዊነት መንፈስና ዘረኛ አስተሳሰብ ስር  በሰደደበት ኢትዮጵያና ለሎች የአፈሪካ ሀገሮች ውስጥ ግን፣ የጋራ ግንዛቤ የመፍጠርን የመሰለ አስቸጋር ስራ የለም። ከሁሉ በላይ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ የጋራ ግንዛቤን ለመፍጠርና  ብሔራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ እንቅፋት የሚሆነው የኢትሮፒያንስ የለየለት ጽንፈኛ አስተሳሰብ ነው። ለመሆኑ እነዝህ ኢትዮሮፕያንስ ማን ናቸው?

ኢትዮሮፕያንስ በኩረጃ ፍልስፍና የተካኑና የምዕራባዊያን የአስተሳሰብ ዘይቤ ተከትለው ማንነታቸውን የሰለቡ ግለሰቦች ናቸው። በተለይ ምዕራቡ ዓለም ባስታጠቃቸው ርዕዮተ-ዓለም ወይም ጽንሰ-ሐሳብ ላይ ተመስርተው፣ በፍፁም የበታችነት ስሜት የራሳቸውን ማንነት (ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ) አብዝቶ የሚጸየፉ ሲሆን፣ በተቃራንው የነጮችን ባህልና ማንነት በለየለት ሁኔታ ያመልካሉ። ኢትዮሮፕያንስ ዘመናዊነትን እንደ ወረደ በመቅዳት፣ ተጨባጨን የሀገሪቱን ሁኔታ ያላገናዘበና የምዕራቡን ዓለም ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ብቻ የሚያስጠብቅ ፖሊስዎችን በመተግበር፣ ሀገራችንን ለእጅ-አዙር ቅኝ-ግዛት ዳርጓታል። ዶ/ር መረራ ጉዲና በትክክል እንደታዘበው “ላለፉት መቶ ሃምሣ ዓመታት ነፃ ሀገር ናት በምትባለዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የኢትዮጵያ መሪዎች ሥልጣን ላይ ለመውጣት ወይም ሥልጣን ላይ ከወጡ ቦኋላ ተደላድሎ ለመቆየት እንድችሉ የውጭ ኋይሎች ጉልህ ሚና ሲጫወቱ እንደነበር ነው…በሀገራችን ፖሊቲካ ውስጥ የውጭ ጣልቃ ገብነት ቋም ክስተት እየሆነ መምጣቱን በውል መንገዘብ ጠቃም ይመስለኛል።” (ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች እና የሚጋጩ ሕልሞች፤የኢህአዴግ ቆርጦ ቀጥል ፖሊቲካ፣ 2008፣ ገጽ 16፣17)

ኢትዮሮፕያንስ ከአውሮፓዊያን ጠበብት በኮረጁት የታሪክ አጻጻፍ ስልት፣ የአንድን ሕዝብ ታሪክ ሙሉ በሙሉ አዋርደው፣ ውሸትን አውነት በማስመሰል ጽፈው ያስተምራሉ። ይህ ከቅኝ-ገዥዎች የተቀዳ የታሪክ ትንተናና አረዳድ እኛ–እነሱ የሚል የሁለታዊነት (dualism) ጽንሰ-ሓሳብ (‹ሴሜን-ደቡብ›፣ ‹ክርስቲያን-አረመኔ›፣ ‹ባንዳ-ኢትዮጵያዊ›፣ ‹እስላም-ክርስተያን›፣ ‹ሴማዊ-ሻንቅላ› ወዘተ) በመፍጠሩ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በአንድነት ኋይሎችና (ultra-right) በብሔርተኞች (ultra-left) መካከል ‹ያላባራ ጦርነት› አስከትለዋል።

በአብዮቱ ጊዜ በብዙ ሊሂቃን ዘንድ የነበረው አንዱ ችግር ‹የኢትዮጵያ ታሪክ›ን የሚተረጉሙበት መንገድ ነበር። በቅርጽና ይዘት የተለያየ ቢሆንም፣ ይህ የታሪክ አረዳድና ልዩነት የመደብና የብሔር ጥያቄን ይዞ ብቅ ብሏል። የ‹ማንነት› ጥያቄን ያመነጨው ኢህአዴግ እንደሆነ የሚሞግቱ ብዙ ሰዎች አሉ። ይህ ትክክል አይደለም። ኢህአዴግ መተቸት ያለበት የ‹ማንነት› ጥያቄን ከመጠን በላይ እንድለጠጥ በማድረጉ ላይ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ‹የማንነት ጥያቄን ያመነጨው ኢህአዴግ ነው› ብሎ መሞገት ግን ከምላስ ላይ ጸጉር እንደመንቀል ይቆጠራል። ተወደደም ተጠላ፣ የመደብም ሆነ የብሔር ጥያቄ በነበረበት ኢትዮጵያ ‹ሁለቱም አልነበሩም› ወይም ‹አንዱ ብቻ ነበር› ብሎ መፈላስፍ በተዘዋዋር ‹በግድ እኛን ሁኑ› የሚል አንደምታ አለው። ‹በግድ እኛን ሁኑ› የሚለውና ከምዕራቡ ‹ዓለም› የተቀዳ አስተሳሰብ በኢትዮጵያ

ምድርም እንደማይሰራ ነው።

የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ በ 1960 ዎቹ የነበረው ትውልድ (‹ያ ትውልድ›)፣ የሀገራችን ባህልና ኀይማኖት ወይም የሕዝቡን ሥነ-ልቡና ግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ ዘመናዊነትን ከእነ አሰስ ገሰሱ በመቅዳት በጊዜው አብቦ የነበረውን የኢትዮጵያ አብዮት አስጠልፏል። ‹ያ ትውልድ› ለውጥ ፈላግ የሆነ ማኅበረሰብ መሆኑ ቢገባንም ቅሉ፣ ለዝህ ታሪካዊ ስህተትና የመጠፋፋት ፖሊቲካ ኋላፍነቱን መውሰድ ይኖርበታል። ይህ ግን የብሔር እኩልነትም ሆነ የሀገር እንድነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በሰከነ መንፈስ ሁላችንንም በእኩልነት የሚታስተናግድ ‹ድሞክራሲያዊት› ኢትዮጵያን ለመፍጠር በቃላት ሊገለጽ የማይችል ተጋድሎ ያደረጉትን ጥቅት ቆራጥ ግለሰቦችን አይመለከትም። በተቃራኒው፣ በሕዝብ ብሶትና እንባ ለማትረፍ ሲሉ፣ አንድም በኢትዮጵያ አንድነት ስም፣ አልያም በብሔር ፖሊቲካ ስም ተነስተው የምዕራባዊያንን የኢኮኖሚ አጀንዳ በስውር በማስፈጸም  ሀገራችንን ለእጅ-አዙር ቅኝ-ግዛት የዳረጓትን አድርባይና ወሮ-በላ ኢትዮሮፕያን ፖሊትከኞችንና ምሁራንን ይመለከታል።

ኢትዮሮፕያንስ የአብጎዳጅነት ስሜት በመላበስ፣ በሀገራችን ውስጥ ለሚፈጠረው ማንኛውም ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የውጭውን ዓለም መፍትሔ ይሻሉ። የኢትዮጵያዊያን ችግር በኢትዮጵያዊያን ‹ብቻ› መፈታት ሲገባ፣ የሦስተኛ ወገን ጣልቃ-ገብነት ይሻሉ። በዝህ ምክንያት፣ ሀገራዊ ችግሮቻችንን በመደማመጥ፣ በመነጋገርና በመግባባት መፍታት አይፈልጉም። የምዕራቡ ‹ዓለም› ርዮተ-ዓለም ለህልና ባርነት ስለዳረጋቸው፣ የተወሳሰበ ታሪክና የማንነት ስብጥር ላላት ሀገራቸው ኢትዮጵያ አንድ ወጥ አመለካከት ብቻ የሚያሰርጽ አካሄድ ይተገብራሉ። ይህንን የለየለት ጽንፈኛ አመለካከት ከሁለት ወገን ማየት ይቻላል፤-

በአንድ በኩል፣ የተለያየ ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ ያለቸውን ሕዝቦች በጉልበት ጨፍልቀው እንድ በማድረግ ‹በግድ እኛን ሁኑ› የሚል ጽንፈኛ አመለካከት ነው። ‹በግድ እኛን ሁኑ› ማለት ሌላ ሳይሆን፣ የራሳችሁን ቋንቋ፣ ባህልና ማንነት ትታቸው የእኛን ማንነት በኋይልና በጉልበት ተቀበሉ ማለት ነው። ይህ አካሄድ ስበዛ አደገኛ ነው። አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ኀይማኖት የሚለው ተረታ-ተረት ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ህያው ምስክር ነው። እንድህ ዓይነቱ ፍልስፍናዊ አመለካከት ገዳፊነት (reductionism) የሚባል ሲሆን፣የሰው ልጅ ስለ ራሱ ንጽረተ-ዓለም (worldview) ያለውን አመለካከት (ቅድሜ-ግንዛቤ—pre-understanding) ተቀዳሚና (primordial) መሠረታዊ (fundamental) መሆኑን ስለሚዘነጋ፣ ለብዙኀ-እይታ (multi-perspective) ፈጽሞ ቦታ የለውም። ስለዝህ ንጹሕ-ኢትዮጵያዊ ከእኛ በላይ ለአሳር የሚለው ትምክህተኛ አመለካከት (ዶ/ር መረራ ይህንን አመለካከት ያለቸውን ሰዎች ‹የኢትዮጵያዊነት የምስክር ወረቀት (certificate) ሰጭና ከልካይ አድርጎ ራሳቸውን የሾሙ› ይሏቸዋል)፣ የዘውግ ጥያቄን ወደ ጥግ መስመር (ultra-left) ከመውሰድ ውጭ የሚያመጣው ፖሊቲካዊ ፋይዳ የለውም። የሚከተለው ትዝብት ለዝህ ሀሳብ ትክክለኛነት አንዱ ምስክር ነው፤ “የንጉሡ መንግስት የኤርትራን ፌደረሽን በማፍረስ ያገኘው ጀበሃና ሻዕቢያ የተበሉ[sic] ተቃዋሚዎችን ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ የሌላቸውን የመጫ ቱለማ የልማት ማኅበር መርዎችንም በማፈን ያገኘው ውሎ አድሮ የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦነግ)ን ነው። ደርግ በተራው፣ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ የሌለውንና በዋናነት በትግራይ ልሂቃን የሚመራውን ኢህአፓን በማፈን ያገኘው ሕወሐትን ነው። በዘመኑ ይሻላሉ በሚባሉ የኦሮሞ ልሂቃን ጭምር የሚመራውንና በኦሮሞ አካባቢዎች ሰፍ ምና የነበረውን መኢሶንን በማፈን ያገኘው ለየት ያለ ሕልም ያላቸውን የኦሮሞ ብሔርተኞችን ነው።”
(ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ ገጽ 23)
በተለይ፣ “ብሔራዊ ስምምነት ላይ መድረስ የሚንችለው አንድ ወጥ አመለካከት/ማንነት ስኖር ብቻ ነው” የሚል እምነት ስበዛ ግልብ አስተሳሰብ ይመስለኛል። አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ኀይማኖት ያላት ሶማሊያ እንኳ ለዝህ አልታደለችም። ለምሳሌ፡- በንገሡ ዘመን የኢትዮጵያ የትምህርት ሚንስቴር ሚኒስትር የነበሩት ሣህሌ ፀዳሉ፣ በ 1933 የሚከተለውን በጣም የተሳሳተ አዋጅ አሳውጀው ነበሩ፡- “ያገር ጉልበት አንድነት ነው፣ አንድነትንም የሚወልደው ቋንቋ ልማድና ሃይማኖት ነው። ስለዝህ ኢትዮጵያ ቀዳማዊ መሆኗን ለማስከበር አንድነቷንም ለማጽናት እስከሁን በቆየው ልማዳችን ተማሪ ቤቶቻችንን አስፍተን ቋንቋችንና ሃይማኖታችንን በመላው በኢትዮጵያ ግዛት በአዋጅ እንዘርጋው፤ ይህ ካልሆነ እስከ መቼውም ድረስ አንድነት አይገኝም። በመላ በኢትዮጵያ ግዛት ለሥጋዊና ለመንፈሣዊ ሥራ ያማርኛና የግዕዝ

ቋንቋ ብቻ በሕግ ጸንተው እንዲኖሩ ሌላው ማናቸውም የአረማዊያን ቋንቋ ሁሉ እንዲደመሰስ ማድረግ ያስፈልጋል።… ሚሲዮኖች ትምህርት ቤቶች እና ሆስፒታሎችንም ቢሆን እንዳይከፍቱ መከልከል ያስፈልጋል፤ ከከፈቱም የውጪ ቋንቋ ማስተማርም ቢሆን እድሉ ለኢትዮጵያውያን መሰጠት አለበት።" (ባህሩ ዘውዴ 2005፡ 132-141) "ማንነቴን የማትቀበል ኢትዮጵያ 99 ቦታ ትበጣጠስ" የሚሉ ግለሰቦች እብድ ስለሆኑ ሳይሆን፣ እንድህ ዓይነቱን ጸረ-ሰው ልጅ መብት አዋጅ ፈጽሞ ስለማይቀበሉ ብቻ ነው!

በሌላ በኩል፣ ያለ ጽንፈኝነት የብሔር ጭቆናንን ማዕከል ያደረገ ፖሊቲካዊ አመለካከት ሲሆን፣ "ምንም ዓይነት የጋራ ታሪክ አልነበረንም" የሚል ተረታ-ተረት ነው። ዶ/ር መረራ ይህንን ወገን "ኢትዮጵያ የሚትባል ሀገር ስም በጆሮየ አልሰማም" ወይም "የታሪክ ሂሳብ እንተሳሰብ" የሚሉ ናቸው ይላቸዋል። በመጀመሪያ፣ በምዕራባዊን ድጋፍ የዛሬይቱን ኢትዮጵያዊ መንግስታዊ ግዛት የፈጠሩ አፄ ምንልክ ነበሩ። የታሪክ አጋጣም ሆነና እነሆ እኛም በዝህ ‹ግዛት› ውስጥ ተገኘንተናል። የመጣንበት መንገድ (አንድ የሆንበት) ግን አንድም በስምምነት ሲሆን፣ ሁለትም በጦርነት ነው። በመሐል አድስ አበባና በአኖለ ላይ የቆሙ ሐውልቶች ለዝህ ሕያው ምስክር ናቸው።

የታሪክ ምንጮች ሁሉ የተዛቡ እንጅ ፍፁማዊ የማይሆኑበትም ለዝህ ነው። ስለዝህ፣ በአንድ ግለሰብ ወይም ሕዝብ ላይ ፍፁማዊ ስምምነት መፈለግ የሰው ልጅ ‹ሕልውና›ን ከቅጡ አለመረዳትን ያመለክታል። የኢትሮፒያንስ ዋና ችግራቸውም ይኸው ነው። የፀጉር ስንጠቃ ክርክር ውስጥ ሳልገባ ከዝ በፊት የጻፍኩትን ሓሳብ በግልጽና በአጭሩ ላስቀምጥ፡- የማንኛውም ግለሰብ ወይም ሕዝብ ታሪክ ምልካምና መጥፎ ገጽታ አለው። ስለዝህ፣ አንድም ፍጹም እርኩስ፣ አልያም ፍጹም ቅዱስ አድርጎ ማቅረብ የአስተሳሰብ ሸርሙጥና ይባላል።

ፍልስፍና ከምዕራባዊያን ‹ዓለም› ለተቀዳ ለእንደዝህ ዓይነት የታሪክ አረዳድና ትንተና ፈጽሞ ቦታ የለውም። ዞረም ቀረ፣ ከ19ኛው ከ/ዘመን መጨረሻ ወድህ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከሌላው ጊዜ የበለጠ ያስተሳሰራቸውና ያቀራረባቸው ብዙ የታሪክ አጋጣሚዎች ነበሩ፤ አሉምም። በአንድ ‹ግዛት› ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ይቅርና፣ ግለሰቦች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚጋሩ ብዙ እሰቶች አሏቸው። ‹የታሪክ ሒሳብ ካልተወራረድን ሞተን እንገኛለን› የሚል ጽንፈኛ አመለካከት ካልተከተልን በስተቀር፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አሁንም አንድ ላይ ሆኖ ይህንን ሀገር የማይገነቡበት ምንም ምክንያት አይታየኝም። ሌላው ቀርቶ የእኛ ስምምነትና አንድነት ከምስራቅ አፊሪካም አልፎ፣ ለአህጉራችን አስፈላጊና በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው።

በተለይ! "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" የሚለው ነገር፣ በአፊሪካ ቀንድ ዘላቂ ሠላም ያሰፍናል ብሎ መደምደም፣ የምዕራቡን ዓለም ፖሊቲካዊ ፍልስፍና በትክክል አለመገንዘብን ያመለክታል። እዝ ላይ እንደ አንድ ዜጋ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድን እውነታ በድፍረትና በግልፅ ለማስረዳት ይወዳለው፤ አሁን በሕግ-መንግስቱ ላይ በግልፅ የሰፈረው አንቀጽ 39 በኢትዮጵያ ምድር ብተገበር እንኳ፣ ኢትዮጵያ በሚትባል ሀገር ውስጥ ዘላቂ ሰላም ይሰፍናል ብሎ ማሰብ፣ ከ2ኛው የዓለም-ጦርነት ወድህ ምዕራቡ ዓለም በአፊሪካ/በኢትዮጵያ ውስጥ የዘረጋውን የእጅ አዙር ቅኝ-ግዛትን በሚገባ ያለማጠንን ያሳያል። የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ፣ ሁለትም ባለመስማማት ለመስማማት (agreeing to disagree) የሚለው ነገር በራሱ ዋጋ አይኖረውም። ይልቅ፣ አፊሪካ/ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ያላትን የዕድገት ፖሊስ እንደገና ማጠን ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ጉዳይ ነው። ብዙ ምሁራን (አፊሪካዊያን/ኢትዮጵያዊያን) ይህንን እውነታ ኢያውቁም ማለት አይቻልም።

የኢትሮፒያንስ (Westernized Ethiopians) ዋነኛ ችግር፣ የኢትዮጵያ ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ የምዕራቡን ዓለም የዕድገት ሞደል የመከተላቸው ጉዳይ ነው።

ኢትየሮፒያንስ የምዕራቡ ዓለም መጠቀምያ ከሚሆኑ፣ ከእድሜ ልክ እንቅልፋቸው ነቅተው እነኝህን ሁለቱን ጽንፈኛ አመለካከቶች ለምን እንደማያስታርቁ ለእኔ ፈጽሞ ግልጽ አይደለም። በዓሉ ግርማ ይህንን አሳዛኝ ጉዳይ እንድ ሲል በግጥም መልክ ገልጾት ነበር፡-

**የአንድ እናት ልጆች**
**በአስተሳሰብ ተጣልተው**
**በአመለካከት ተለያይተው**
**የሚያስተርቅ ጠፍቶ**
**የእብድ ገላጋይ በዝቶ**

ዛሬም አንዱ ወገን ሌላውን ከመውቀስ ውጭ የጋራ አጀንዳ ቀርጾን፣ ለሀገራችን ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዘላቅ መፍትሔ ማመንጨት ‹አልቻልንም›። ዝለዝህ አንድ ላይ ‹ማልቀስ› እንጅ አንድ ላይ መስራት አልተቻለም!! የኢትዮጵያ ‹ታሪክ› እስከገባኝ ድረስ፣ የሥነ-ልቦና ጥቅም ካልሆነ እንጅ፣ ባለፉት ሥርዓቶች ሆነ በአሁኑ ወክት በኢኮኖም ረገድ አንድ ወገን ብቻ ተጠቃም ነበር ብሎ መፈላሰፍ፣ ለፖሊቲካ ፍጆታ ክልሆነ በስተቀር ከተጨባጩ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር የተገናኘ አይደለም።

ኢትዮሮፐያንስ ግን በአጉል ተመጻዳቅነት ‹ወዝ-አደር-ላብ-አደር› ‹ሀገር-ሕዝብ› ‹እናሸንፋለን-እነቸንፋለን› ‹ግለሰብ-ቡድን› ‹ግደታ-ነፃነት› ወዘተ የሚሉ ጽንሰ-ሐሳቦችን አንዱ የሌላው ተቃራን አድርጎ ለማቅረብ ሞከሯል። ይህ የፅጉር ስንጠቃ ክርክር ዛሬም ለእኛ ትውልድ ተርፎ የማንነት ግራ መጋባት ውስጥ ከቶናል። ‹ሀገርና-ሕዝብ› ወይም ‹ግለሰብና-ቡድን› ወይም ‹ግደታና-ነፃነት› የአንድ ሣንትም ሁለት ገጽታ መሆኑ እየታወቀ፣ ‹ከአንበሳውና ጐፈረው የትኛው ይቀድማል› ብሎ መፈላሰፍ ለተራበው ዜጋችን ዳቦ ይሆናል ብዬ አላስብም።

በጣም የሚገርመው፣ ‹ያ ትውልድ› የአሁኑን ትውልድ (በተለይ ወጣቶችን) ግለብ አስተሳሰብ ብቻ እንጅ፣ የበሰለና የጤራ እውቀት እንደሌላቸው አድርጎ ለመሳል ይሞክራል። የትኛው ትውልድ ‹እንደ ጉንዳን ከአንገት በላይ እንደሚወፍር› ለታሪክ ልተወውና፣ ‹ያ ትውልድ› እነደዝህ ዓይነት ወቀሳ በእኛ ትውልድ ላይ ለመሰንዘር የሞራል ብቃት እንደሌለው ለማረጋገጥ ይወዳለው። ኢትዮሮፐያንስ ሆይ! ለመሆኑ ምን ዓይነት ሀገር ነው የተረከብናችው? አብዛኞቻችሁ ለሕዝብ ሰቆቃና ስቃይ መፍትሔ ከማፈላለግ ፋንታ፣ ለግል ጥቅማችሁ ሲትሉ አይደለም እንደ የጥሎ ማለፍ ፖሊቲካ ውስጥ የገባችውት? አንድ መንግስት አልፎ በሌላ ሲተካ፣ ማን ነበር ወይም ማን ነው ገንዘብና ስልጣን ፍለጋ የፖሊቲካ ዥዋዥዌ ስጫወት የኖረው? መስታወት ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው አስቀድሞ ድንጋይ መወረወር የለበትም።

አውነት ነው የእኛ ትውልድም (እዝ ላይ የራሴ ‹ድንቁርና› ይቀድማል) የራሱ የለየለት ደካማ ጎን አለው። ይሁን እንጅ፣ የሁላችን ድክመት መቅረፍ የሚንችለው በኢላፍ-ኢላሜ ፍለስፍናዊ ዜደ (የመደማመጥ፣ የመግባባትና የመነጋገር ፍልስፍናዊ ውይይት—Ilaa-fi-Ilaamee philosophic method of enquiry) በማዳበር እንጅ፣ እርስ በርስ በመወቃቀስና በመናናቅ አይደለም። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የምርምር ተቋማት አንድም ከትምክህተኝነት፣ አልያም ከጠባብነት የጸዱ ባለመሆናቸው፣ ‹ገለልተኛ› ሆኖ የጠራ ጥናት ማካሄድ አስቸጋር የሚሆነው በዝህ ምክንያት ይመስለኛል። ህልናና ሆድ ፈጽሞ መስማማት ስለማይችሉ፣ አንዳንድ ጊዜ በትምህርተ ዓለምም ‹ብቸኛ› መሆን አይከፋም።

ስለዝህ፣ እያንዳንዱ ትውልድ እራሱን መመርመር አለበት። የዛሬው ወጣት ስለ አህምሮውና ማንነቱ ሳይሆን ስለ አለባበሱና ስለ መኪና ብቻ ለምን አብዝቶ እንደሚጨነቅ ወይም ስለ ሕዝቡ ሰቆቃና ስቃይ ሳይሆን ስለ ዶላርዝምና ፔንሲዮን አብዝቶ የሚያስቡ የመንግስት ባለሥልጣንናትና የኀይማኖት አባቶች ለምን እንደ አሸን መፍላት እንደቻሉ መመለስ ያለበት የአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ‹ያ ትውልድም› ጭምር መሆን አለበት! ኢትዮሮፐያንስ ከእኛ ትውልድ ጋራ የሚታረቁበት ጊዜ አሁን ይመስለኛል። የውሃ ቀጠነ ክርክር ትተን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቤ ዘላቂ የፖሊቲካ መፍትሔ ማፈላለግ ይኖርብናል። ሕዝብን በሃይመኖትና በብሔር እያከፋፈልን ማፋጀት፣ የምዕራቡን ‹ዓለም› ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚዊ ጥቅም ከማስጠበቅ ውጭ ለብዙኀኑ ኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስገኘው ጥቅም ፈጽሞ እንደሌለ መታወቅ ይኖርበታል። በአጠቃላይ በእሳት የመጫወት አባዜ ለሁላችን የሚበጅ አይመስለኝም።

Yoseph Mulugeta Baba was born in Konchi/Nekemte, Ethiopia. He holds a B.A, M.A, and Ph.D. degrees in Philosophy from The Catholic University of Eastern Africa (CUEA), Nairobi-Kenya. He also holds a B.D, in Sacred Theology (Magna Cum Laude Probatus) from Pontifical Urbaniana University, Rome. He has taught philosophy at CFIPT, Addis Ababa, Ethiopia. His research interests

involve: Metaphilosophy, Oromo Philosophy, Continental Philosophy, Post-colonial African Philosophy, Sage Philosophy, and Post-modernism. His publications include, Metaphilosophy or Methodological Imperialism? (2015); Philosophical Essays (2016); The Oromo Concept of reality: Epistemological Approach (2016); የኢትዮሮፒያንስ የአስተሳሰብ ቅሬ፤ ‹አበበ በሶ በላ› vs ‹ጫላ ጩቤ ጨበጠ› (2017); Kana Dubbiin (2017). His book titled, Remembering Great African Thinkers, is forthcoming. He can be reached at: kankokunmalimaali@gmail.com